# amnesty international

## ኦመንስቲ ኢንተርናሽናል

# የኢትዮጵያና የኤርትራ

# የሰብዓዊ መብትና አጀንዳ

ሕዳር 1983 ዓ.ም. (1991)

AI INDEX: AFR 25/09/91/AMHARIC

AMNESTY INTERNATIONAL
INTERNATIONAL SECRETARIAT, 1 EASTON STREET
LONDON WC1X 8DJ, UNITED KINGDOM

# ጥቆማዎች

1- መካከለኛ እስር ቤት (ካርቸሌ) አዲስ አበባ

2- ዓለም በቃኝ (መጨረሻ ዓለም) ጽሑ የእስር ክፍል በመካከለኛው እስር ቤት ውስጥ አዲስ አበባ

3- በጣም የሚፈራ ክፍል 7 ቁጥር ማዕከላዊ የጸጥታ እስር ቤት አዲስ አበባ ውስጥ የእጅ ብረት በሩ ላይ የተንጠለጠለበት

4- መሰቃየት - የውስጥ እግርን መደብደብ (ማስተካከል)

5- "በርሙዳ ትሪያንግል" ብዙ እስረኞች "የሚጠፋበት" ከድር አውሮፕላን ማረፊያ አጠገብ የሚገኝ ሚስጥራዊ እስር ቤት። የአመንስቲ ኢንተርናሽናል ወኪሎች ሐምሌ 1983 ዓ.ም. (1991) ፊልም ሲያነሱና ቃል መጠይቅ ሲያደርጉ ታይተዋል።

6 እና 7- ቄስ ጉዲና ተምሳ (ግራ) የኢትዮጵያ ወንገላዊት ቤተ ክርስትያን ሐላፊ በ1972 ዓ.ም. (1979) ጠፍቶ የቀረው። ባለቤቱ ፀሃይ ቶሎሳ (በቀኝ) ከ 1973 ዓ.ም. (1980) እስከ 1982 ዓ.ም. (1989) ድረስ የታሰረች።

8- ካሳ ወልደ ማሪያም የእርሻ ሚኒስተር በፊት ደግሞ የዩኒቨርስቲ ፕሬዘዳንት የነበረ በ 1967 ዓ.ም. (1974) የታሰረ ሐምሌ 1972 ዓ.ም. (1979) የጠፋ።


9- አብነ ቲዎፍሎስ (ቲዎፊሎስ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ፓትሪያርክ በ 1969 ዓ.ም. (1976) ታስረው በ 1972 ዓ.ም. (1979) የጠፉ።




1



2



3



4



5


6


7


8


9

# የ ኢ ት ዮ ጲ ያ ና የ ኤ ር ት ራ
# የ ሰ ብ ኣ ዊ መ ብ ት ና አ ጀ ን ዳ

**መግቢያ**

አረሜናዊ ጭቆና በኢትዮጲያ ውስጥ ከሰፈነ ከሃያ ዓመት በላይ ሆኖታል። የፕረዚደንት መንግስቱ ሃይለማሪያም በግንቦት 21, 1983 ዓ.ም. (1991) በድንገት ማምለጥ እንደዚሁም ከሳምንት በኃላ የኢትዮጲያ ወታደሮች በተጻራሪዎቹ ቡድኖች መሸነፍ ለሰላሳ ዓመት ኤረትራ ውስጥ የተካሄደው የርስበርስ ውግያና ከ 1967 ዓ.ም. (1974) አብዮት በኃላ የነበሩ የተለያዩ ጦርነቶች መጨረሻ የሰብኣዊ መብት መገፈፍ ሆነ።

የኢትዮጲያ ህዝብ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢ.ህ.አ.ዲ.ግ) በተጋድሎ ሓርነት ህዝብ ትግራይ (ተ.ሓ.ህ.ት) መሪነት በግንበት 28 ቀን 1983 ዓ.ም. (1991) የኢትዮጲያ ዋና ከተማ አዲስ አበባን ተቆጣጠሩዋት። ከጥቂት ቀኖች በፊት በአሜሪካ ሊቀመምንበርነት የተፈጸመው የሰላም ስምምነት መሰረት ኢ.ህ.አ.ዲ.ግ ግዚያዊ አስተዳደር መሰረተ። ይህ ደግሞ በነሐሴ 1983 ዓ.ም. (1991) ሰፊ የመሸጋገሪያ መንግስት መስረቶ ብዙ ፓርቲዎች ለምርጫው እንዲገቡ መንገድ ከፈተ። ኢ.ህ.አ.ድ.ግ እና የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር (ኦ.ነ.አ.ግ) ሌሎችም የፕረዚደንት መንግስቱን መንግስት የተጋደሉ ሃይሎች እንዲሁም የፖለቲካና የቀበሌ ሃይሎች የተካፈሉበት 87 ተካፋዮች በ 1980 ዓ.ም. (1987) የነበረውን ሕገ መንግስት በመለወጥ ጊዜያዊ ሕግ በማርቀቅ የተለያዩ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች መጠበቅን አረጋገጠ።

በመጨረሻ ግንቦት 1983 ዓ.ም. (1991) ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ህ.ግ.ሓ.ኤ) አስመራን በመያዝ ኤርትራን በሙሉ ተቆጣጥሮ ግዜያዊ መንግስት አወጀ። በዚህ ደግሞ ኤርትራ በ ኢ.ህ.አ.ደ.ግ የኢትዮጲያ መሸጋገርያ መንግስት

ታዋቂነት ያገኘች የተለየች ሀገር ሆነች። ከሁለት ዓመት በኃላ በዓለም አቀፋዊ ታዛቢነት ሪፈረንደም ተደርጎ የመጭጠው አድልዋን እንድትወስን ይደረጋል።

በችግር የተዋጠ አገር ውስጥ በአዲስ አበባ አዲስ ምእራፍ ተከፈተ። በአሜሪካ ሊቀመንበርነት በኢትዮጲያ ሕዝብ አብዮታዊ ዲሞክራሳዊ ግንባር (ኢ.ህ.አ.ደግ) በህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ህ.ግ.ሓ.ኤ) እና በኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር (ኦ.ነ.አ.ግ) መካከል ለንደን የተደረገው ድርድር በዚህ ሳምንት ጦርነትን አስወግዶ ወደ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የምያመራ ኢትዮጲያና ኤርትራ ውስጥ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም ተስፋ ሰጠ። ይህ ደግሞ ከዚህ በፊት ከነበረው አስተሳሰብ ወጥተው የሰብአዊ መብት ለመጠበቅ ዋና አርእስት አድርጎ ለብዙ ግዜ ሲሰቃይ ለቆየው ሕዝብ ተስፋ ሰጠው። ለ 17 ዓመት ጦርነትና ርሀብ አገሪቱን አፈረሳት። አንድ ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ በርሃብ ተጨርሰዋል። በመቶ ሺ የሚቆጠሩ በርስበርስ ውግያና በፖለቲካ ግርግር ሞተዋል። ከሚልዮን በላይ የሚበልጡ ሰዎችም ከአገራቸው የተሰደዱት ከርሃብና* ደም መፍሰስ ለማምለጥ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ምክንያት በመገደድ* ከዘመቻ እዲሁም በግዳጅ ሌላ ቦታ ከመስፈር ለማምለጥ ጭምር ነው።

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ መካከል መሰረታዊ ሰብአዊ መብት ሊዘነጋ ይቻላል። ይህ ተሻሽሎ የቀረበ ሪፖርት ለ 17 ዓመት ያህል ከነበረው ጭቆና አዲስ የስረኞች ምስክርነትና ከሰኔ እስከ ሕዳር 1983/84 ዓ.ም. (1991) የተለወጠ የሚያመለክት ነው። አመንስቲ ኢንተርናሽናል ይህን ጽሑፍ ያቀረበው ለሁሉ ሰው በመንግስቱ የሚመራውን መንግስት የሰብአዊ መብት መዝገብ ለመክፈት ብቻ ሳይሆን እነዚህ አሁን አገሪቱን የሚመሩትን ለሰብአዊ መብት ቅድሚያ እንዲሰጡት ለማስተሳሰብ ነው። ሰብአዊ መብት የገፈፈው መንግስት ያለፈውን ሁሉ ችግር አሽከሞ አሁን ከፈረሰ በኋላ ተሰብአዊ መብት መዘንጋት የለበትም። አንገሽጋሹ ሰብአዊ መብት መጣስ ፕረዚደንት መንግስቱ ስልጣን በነበረበት ጊዜ ዋና ምልከቱ እንደነበረ አንደገና እንዳይመለስ የሚያረጋግጥ መሰረታዊ ለውጥ መደረግ አለበት።

በዚያ ጊዜ በሺ የሚቆጠሩ የነበረውን መንግስት የሚቃወሙ ያለ ፍርድ ጥፋታቸው

ሳይነገራቸው ታስረው ነበር። ከነዚህም ውስጥ የሕሊና እስረኞች ማለት ወንዶች፣ ሴቶች፣ ህፃናት፣ በእምነታቸው፣ በጾታቸው፣ በቆዳቸው ቀለም፣በቋንቋቸው መሰረት ረብሻ ያደርጉ ይታሰሩ ነበር። እስር ቤትም ውስጥ ወንጀለኞችና የፖለቲካ እስረኞች ማሰቃየትና ሰብአዊ ባልሆነ አገባብ መቅጣት የእለት ተግባራቸው ነበር። በመቶ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች ሲገደሉ በሺ የሚቆጠሩ ደግሞ የት እንደደረሱ ሳይታወቅ የጠፉ ነበሩ። በመጨረሻ በ 1963 ዓ.ም. (1970) በ "ቀይ ሽብር " ጊዜ ጸረ አብዮተኞችን ለማጠፋት ተብሎ ብዙ ሰዎች ተገድለዋል። የኢትዮጲያ ወትደሮች በሰላማዊ ህዝብ መኖርያ ላይ አውቆው ቦንብና ናፓል በመጣል ብዙ ሰዎች ጨርሰዋል። ሰላማዊ ህዝብና በጦርነት የተማረኩ በብዛት እንደተገደሉ ሁል ጊዜ ሪፖርት ይተላለፍ ነበር።

የኢትዮጲያ መንግስት ባለስልጣኖች ግን በተደጋጋሚ የሚያደርጉትን የሰው መብት መጣስ ወይም ማሰቃየት ያልተረጋገጠ የፖለቲካ ፕሮፖጋን ነው እንጂ እኛ የፖለቲካ እስረኛ የለንም በማለት ይክዱ ነበር። የወደቀው መንግስት ያደርገው የነበረውን ማሰቃየት በመሸፈን ሳይቀበለው ለ 20 ዓመታት አፍኖታል።

በነዛ ሰፊ መሬት በሚቆጣጠሩት ተቃዋሚ ቡድኖችም የሰብአዊ መብት ተጥሰዋል። ህ.ግ.ሓ.ኤ አብዛኛውን የኤርትራ ክፍል ያስተዳድራል። እንዲሁም ኢ.ህ.አ.ደ.ግ ትግራይንና በቅርብ ጊዜ የተያዙ ቦታዎችን ያስተዳድራል። በነዚህ ተቃዋሚዎች ቡድን ኢትዮጲያ ውስጥ የሚታየው የሰው መብት መጣስ በወታደሮች ከተደረገው ሲመዛዘን ቁጥሩ በጣም ዝቅ ያለ ነበር። ይሁን እንጂ አመንስቲ ኢንተርናሽናል የሚያገኘው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ማሰር፣ ማሰቃየት፣ ሰው አፍኖ መውሰድና የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን መግደል በመጠኑ በተቃዋሚዎች ቡድንም ይታይ እንደነበር ነው። እላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ተቃዋሚ ቡድኖች ብዙ ውስጣዊ ምስቅልቅል ደርሶባቸዋል። የመንግስት ስልጣን ከሚቃወሙ ሀይሎች ጋርም ግጭት አድርገዋል።

አዲስ የፖለቲካ ሀዋህው ለሰብአዊ መብት ምቹ የሆነ ይመስላል፤ይሁን እንጂ አዲስ የሰብአዊ መብት መጣስ በሚታዩበት ወቅት ጉዳዩ የተለየ ተኩረት ያስፈልገዋል። አመንስቲ ኢንተርናሽናል አሁን በኢትዮጲያና በኤሪትራ በስልጣን ላሉት በዓለም የተደነገገውን የሰብአዊ መብትን ለዘላቂ እንዲጠብቀት ያስተሳስባል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ሕጋዊና ለዘላቂ የሚያሰራ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ያለፈው ጭቆናና የሰውን መብት መጣስ ፈጽሞ መመለስ የለበትም።

## መነሻ

በ 1967 ዓ.ም. (1974) በወታደራዊ ኃይል የተጀመረው እንቅስቃሴ ለ 44 ዓመት ኢትዮጲያን ይገዛ የነበረውን ንጉሥ ሃይለስላሴን ከስልጣኑ አወረደው። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት አዲሱ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ሰብአዊ መብት በመጣስ ብዙ በደል አድርጓል። ከአብዮቱ በኃላም በመቶ የሚቆጠሩ የድሮ ባለስልጣኖች ታስረው የነበሩ ያለ ፍርድ ተገድለዋል። ደርግ (ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ተብሎ የሚታወቀው) በመስከረም 1967 ዓ.ም. (1974) ስልጣን ከጨበጠ ከሁለት ወራቶች በኃላ 59 እስረኞችና ያገሪቱን መሪ ገደለ። ብዙ እስረኞች በ 1972 ዓ.ም. (1979) የት እንደደረሱ ሳይታወቅ ጠፍተው ሲቀሩ ሌሎች ደግሞ በየጊዜው ተለቀዋል። ከተለቀቀት ውስጥ ሦስቱ የንጉስ ኃይለስላሴ የልጅ ልጆች ከ 15 ዓመት በኋላ ተለቀቀ፤ ንጉስ ኃይለስላሴ እርሱም ከስልጣኑ ከወረደ ከአንድ ዓመት በኃላ አቤተ መንግስት ውስጥ ተገደለ። ደርግን ለመገልበጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩት ሆነ ብለው ተገድለዋል። ከ 1970 ዓ.ም. (1977) እስከ 1972 ዓ.ም. (1979) የግራ ክንፍ ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት በማለት ብዙ ደም የፈሰሰው ጨካኝ "ቀይ ሽብር" ተብሎ በተጠራው አልቂት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰላማዊ ሰዎች በእስር ቤትና በየ ባቡር መንገድ ላይ ተገድለዋል።

ኢትዮጲያ ውስጥ እንቅስቃሴ የተፈጠረው የእርስ በርስ ጦርነት በነበረበት ጊዜ ነው እንቅስቃሴ የተፈጠረው። የኤርትራ ተቃዋሚዎች ለነጻነታቸው ከ1952 ዓ.ም. (1960) ጀምሮ ይታገሉ ነበር። ሌሎችም የትግራይና የኦሮሞ

ተቃዋሚዎች አገሪቱን በበለጠ ወደ አዘቅት አስገብዋት። በዚህ የወታደራዊ ግጭት ሳቢያ ብዙ የሰብአዊ መብቶች ጉድለት በወታደሮች አንዳንድ ጊዜም በተጣራሪዎች ቡድን ተፈጽሞአል። በተለይ መንግስትን የሚዋጉ ጎሳዎችም ሆነ የክፍለ ሃገር ቡድኖች በኤርትራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሞ ውስጥ ፍርደ ገምድል የሆነ በቀል ደርሶባቸዋል። አብዛኛው በመንግስት ወታደሮች በኩል ቢሆንም ተቃዋሚ ቡድኖችም በደል ፈጽመዋል። ከ 1970 ዓ.ም. (1977) እስከ 1971 ዓ.ም. (1978) ኦጋዴን ውስጥ በኢተዮጲያና በሶማሌ መሀከል በተደረገው ጦረነት በሁለቱ ወገን ብዙ የሰብአዊ መብቶች ተጥሰዋል።

እንደዚህ በመሳሰሉ ግጭቶች በሚበዛበት ወቅት እንዲሁም ዲሞክራሲ የሚጠብቁ ድርጅቶች በሌሉበት አስተያየት መስጠት ሆነ ተቃውሞ ለመንግስት መግለጽ ፈጽሞ የማይቻል ነበር። 1980 ዓ.ም. (1987) የተደነገገው የፖለቲካዊ ለውጥ ያዘለው ሕገ መንግስትና በ 1983 ዓ.ም. (1990) ለታወጀው አዋጅ ቃል ገቡ እንጂ በስራ ላይ አላዋሉትም። ከ 1967 ዓ.ም. (1974) ለውጥ ከተደረገበት ጀምሮ እስከ 1973 ዓ.ም. (1980) ድረስ የነበረውን መንግስት ለተቃወሙ ሰዎች "የመጥፋትና" ከሕግ ውጭ የሆነ መገደል እንዲሁም ያለ በቂ ምክንያት እስራት ያስከትልባቸው ነበር። እንድዚህ ዓይነት ሁኔታ መንግስቱ እስኪገለበጥ እስከ 1983 ዓ.ም. (1991) ድረስ ቀጠለ።

## ፖለቲካዊ እስራት

ኤርትራዊያን አዲስ አበባ ውስጥ በጸጥታ ፖሊሶች ታስረው ያለአግባብ እንደሚገላቱ አንድ ከእስር ቤት የተፈታ እስረኛ ለአምንስቲ ኢንተርናሽናል አመለከተ። " ይሄ ደሞ ትግርኛ የሚናገርና ስሙ ለየት ያለ ከሆነ በቀበሌ ተጠቁሞ ኤርትራዊ ነው በመባል ይታሰራል። የበላይ ባለስልጣኖችና የጸጥታ ሀላፊዎች ሳይቀሩ በዚህ ዓይነት አግባብ ይታሰሩ ነበር።"

ባለፈው 17 ዓመታት ውስጥ ከ 10 ሺ እስከ 100 ሺ የሚቆጠሩ በፖለቲካ ምክንያት የታሰሩ ነበሩ። ከነዚህ መሃል የሕሊና እስረኞች የሚካዬድ ያለውን

ግድያ የሚቃወሙ ሲሆኑ የታሰሩበት ምክንያት ደግሞ የፖለቲካ አስተያየታቸውና ዘራቸውን በሚመለከት ጉዳይ ነበር። ምናልባት አንዳንዶቹ ደግሞ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ብረታዊ እንቅስቃሴ ከሚያካሂዱ ማሕበራት ግኑኙነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። እንደዚህ ያለ አግባብ በማሰቃየትና በማስለፍለፍ ምልከት አግኝተናል በማለት ያለምንም ማስረጃ ያሰሩዋቸው ነበሩ።

ከነዚህ በፖለቲካ ምክንያት ከታሰሩት ጥቂቶች ከስ ቀርቦባቸው ፍርድ ቤት ቀርበው አልተፈረደባቸውም ነበር። አብዛኛዎቹ ግን ላልተወሰነ ጊዜ በጹሁፍ ባልሰፈረ የጸጥታ ባለስልጣኖች ትዕዛዝ ተፈርዶባቸው የታሰሩ ነበሩ። የጸጥታ ባልደረቦች መጀመሪያ በየክፍላቸው አስረው ያቆየዋቸዋል። "ለምሳሌ አዲስ አበባ ውስጥ እንደ ማዕከለኛ (ፎቶ 3 ገጽ ii)" አስመራ ውስጥ ማሪያም ግንቢ። በዚህም መቆያ ቦታ ማሰቃየትና ማስለፍለፍ የተለመደ ነበር። ሌሎች ብዙ የመታሰሪያ ቦታዎችም ነበሩ። ለምሳሌ " በርሙዳ ትራያንግል" (ፎቶ 5 ገጽ ii) አዲስ አበባ ውስጥ አሮጌ አይሮፕላን ማረፊያ አጠገብ የሚገኝ ቪላ ቤት ነው። እዚያ የሚታሰሩ ብዙ ጊዜ ጠፍተው ይገኛሉ። ከነዚህ ጥቂቶቹ በሚስጥር ኮሚቴ ላልተወሰነ ጊዜ ተፈርዶባቸው ወደ ዋናው እስር ቤት ይተላለፋሉ፣ ለምሳሌ አዲስ አበባ ውስጥ እንደ መሃከለኛው እስር ቤት (ካርቸሌ) (ፎቶ 1 እና 2 ገጽ i) አስመራ ውስጥ ሰንበል እስር ቤት። እነዚህ እስር ቤቶች የያንዳንዱን ሰው ጉዳይ በመዝግብ የሚያዙበት ቦታ ነበሩ። ይህ መዝገብ የሚያመለክተው እስረኛው ለምን እንደታሰረ ብቻ ነው። የፖለቲካ እስረኛ እራሱን ከስቃይና ከጭንቀት ለማዳን ብሎ የለፋለፈውን በሕግ ሊመልሰው መብት አልነበረውም። ይሁን እንጂ የጸጥታ ሚስጥራዊ ኮሚቴ ጉዳዩን እንደገና በማየት ምህረት ሊያደርግለት ይችል ነበር።

ከ 1970 ዓ.ም. (1977) እስከ 1971 ዓ.ም. (1978) " በቀይ ሽብር " ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች የት እንደደረሱ ሳይታወቅ " ጠፍተው " የቀሩበት ምክንያት ያለ አግባብ በማሰቃየትና ህክምና ለሚያስፈልጋቸው በመከልከል የሞቱ ናቸው ብሎ አመንስቲ ኢንተርናሽናል ያምናል። ኤርትራ ውስጥ 1973 ዓ.ም. (1980) ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር። ከእስረኞች ጥቂቶች

ምህረት ተደርጎላቸው ሲያበቃ የመንግስቱ ግዛት በ 1983 ዓ.ም. (1991) ከተገለበጠ በኃላ ግን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ገና እስር ቤት ይገኙ ነበር። ምናልባት አብዛኛዎቹ እስከአሁን ሳይፈቱ አይቀሩም ዳሩ ግን ጥቂቶቹ ተገድለዋል የሚል ሪፖርት አለ።

ወታደራዊ እንቅስቃሴ ባለበት ቦታዎች ማለትም ኤርትራ* ትግራይ* ኦሮሞ* የሚገኙ በርከት ያሉ ሰዎች ያለ አግባብ እንዲታሰሩና እንደ ፖለቲካ እስረኞች እንዲቆጠሩ ይደረግ ነበር። ከነዚህም ውስጥ የመንግስት ባለስልጣኖችና* የፓርቲ አባሎች* አስተዳደርን በመንቀፍ የተባበሩት ምንግስታት ተማሪዎች በሀይል የመለሱዋቸው ጥገኞች* የውጭ አገር ዜጋዎች* የቀድሞውን መንግስት የሚደግፉ የውጭ አገር የነፃነት ተንቀሳቃሾች* ይገኙበታል።

ብዙ ኤርትራውያን ነጋዴዎች አዲስ አበባ ውስጥ ያለ አግባብ ለ 6 ዓመታት ታስረው ነበር። የታሰሩበት ምክንያት ደግሞ ከህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ጋር ግኑኝነት ይኖራቸዋል በሚል ጥርጣሬ ይሆናል እንጂ ለምን እንደታሰሩ መግለጫ አልነበረም።

ባለፈው 17 ዓመታት ኤርትራ ውስጥ ብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ከህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብሎ በጸጥታ ፖሊሶች ይታሰሩ ነበር። አብዛኛዎቹ ደግሞ ያለ አግባብ ያለ ፍርድ ስለ ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ በማለፋለፍ ያሰሩዋቸው ነበር። ከነዚህም በተደጋጋሚ የታሰሩና የተለፋለፉ አሉ።

በመጀመሪያው 1983 ዓ.ም. (1991) በአስመራ* ከረን* ደቀምሓሬ* አሰብ* ብዙዎቹ ኤርትራ ውስጥ ታስረው በመሰቃየት ይመረመሩ ነበር። ከነዚህ አስመራ ውስጥ ከታሰሩት በለው ገብረመድህን ወደ ውጭ አገር ለጉብኝት ሄዶ የተመለሰ* ገብረሃዋሪያት ቂስ ዓንደሚኪኤል ሸማግሌ ገበሬ* ፍቱን አስረስ የፋብሪካ ሃላፊ* በኪት ሃብቶም የበጁክ ከንቲባ ይገኙበታል። እነሱም ምናልባት እስከ 1983 ዓ.ም. (1991) ሕዝባዊ ግንባር አስመራ እስኪ ገባ ድረስ ያልተፈቱ

ናቸው።

ሁል ጊዜ ሕዝባዊ ግንባር ባደረጋቸው ጦርነቶች ድል ሲያደርጉ ብዙዎች ኤርትራዊያን ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ ይታሰራሉ። በ 1975 ዓ.ም. (1982) ለመንግስቱ ሳይሳካለት የቀረው "የቀይ ሽብር" ዘመቻና በመጋቢት 1981 ዓ.ም. (1988) ሕዝባዊ ግንባር በድል አድራጊነት ናቅፋን ሲቆጣጠሩዋት በመቶ የሚቆጠሩ ኤርትራዊያን ታስረው ነበር። ከነዚህ ዋናዎች የሕዝብ አገልጋዮች፣ አስተማሪዎችና ነጋዴዎች ይገኙበታል።

በመቶ የሚቆጠሩ የኦሮሞ ተወላጆች ከኦሮሞ ነፃ አውጪ ማሕበር ጋር ግንኙነት አላችሁ ተብለው ታስረዋል። 12 የሴቶችና ተቃዋሚዎች ከ 10 ዓመት በላይ ከታሰሩ በኃላ በአመንስቲ ኢንተርናሺናል እንደ ሕሊና እስረኞች የታወቁ ግንቦት 1983 ዓ.ም. (1991) ድረስ ታስረው ነበር። ከእነሱም ውስጥ ዳኜ ቢላ የተባለ የወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የልማት ኃላፊ በቃሊቲ አዲስ አበባ አጠገብ ያታሰረ* ደምሴ ከበደ የኢትዮጲያውያን የንግድ ማህበር ሊቀ መንበር በእስር ቤት የታመመ* ሙሉጌታ ሞሲሳ የእህል ቦርድ ባልደረባ በማዕከላዊ እስር ቤት አዲስ አበባ ውስጥ በሕመም መሰቃየት ላይ የነበረ* ወልደ ዮሃንስ ሁንዴ በማስታወቂያ ሚኒስቴር የኦሮሞኛ ጋዜጣ እንደ ጋዜጠኛ ሆኖ ይሰራ የነበረ* ባሪሳ በማዕከላዊ እስር ቤት በሳንባ ነቀርሳ መሰቃየት ላይ የነበረ* ይገኙበታል።

በመቶ የሚቆጠሩ ትግሬዎች በትግራይና በአድስ አበባ ውስጥ ከትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ግንባር ጋር ግኑኝነት አላችሁ በሚል ጥርጣሬ ታስረው ይገኛሉ። ከነዚህ ማንም ለፍርድ የቀረበ የለም። እስከ ግንቦት 1983 ዓ.ም. (1991) ለ 12 ዓመት ያህል ትግሬዎች የፖለቲካ እስረኞች ሆነው በወይን ቤት ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ አማረ ዶሬ የአድዋ አስተዳደር* ብርሃኑ ማሞ የመቀሌ ከንቲባ የነበረ* ጌታቸው በላይ አስተማሪ* ግርማይ በርሄ የውስጣዊ ንግድ ሚኒስተር ሰራተኛና የታወቀ ባህላዊ ተጫዋች* ፀሀየ ደባልቀው በጋዜጣና ቴሌቪዥን በተለይ ደግሞ በአማረኛ ለሚቀርበው አዲስ ዘመን ለተባለው ጋዜጣ ጸሐፊ

ይገኙበታል። ሌሎች ትግሬዎች የፖለቲካ እስረኞች እስከ ግንቦት 1983 ዓ.ም. መጨረሻ (1991) ለ 12 ዓመት የታሰሩ ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ ለመጥቀስ ሰለሙን ገብረአምላክና አረጋይ ገብረእግዚአብሔር የአድስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች* ሃይለ ሓለፎም ወታደር ናቸው። ሌሎች ከ 1973 ዓ.ም. (1980) ጀምር በእስር ቤት ያሉ ለመጥቀስ አሰፋ አብርሃ ኢንጂነር የምርት ጥራት ኃላፊ እስከ አሁን ድረስ እስር ቤት ይገኛል። አብዛኛዎቹ ትግሬዎች በመጀመሪያው 1974 ዓ.ም. (1981) የታሰሩ ከብዙ ወራቶች በኃላ የተለቀቁ ናቸው። የጥቂቶቹ ደህንነት በሚያጠራጥር ሁኔታ ላይ ይገኛል።

እስከ 1983 ዓ.ም. (1991) ከእስረኞች ውስጥ ሶስት ሴቶች ነበሩ። እነሱም ንግስቲ ጊዮርጊስ በወታደሮች ችሎት ያለ ሕግ ከ 1970 ዓ.ም. (1977) ጀምራ አድሜ ልክዋን እስራት የተፈረደባት* ታደለች ኃይለ ሚካኤል በ 1972 ዓ.ም. (1979) በሚስጥር ለሞት የተፈረደባት ስትሆን በዚያን ጊዜ ግን እርጉዝ ስለነበረች የሞት ፍርዱዋ ለአድሜ ልክ እስራት የተለወጠላት* ገነት መብርሃቱ የተባበሩት መንግስታት ሰራተኛ ከ 1982 ዓ.ም. (1989) ጀምራ ያለ ፍርድ የታሰረች ነበሩ።

12 ዓመታት በአገሪቱ ለነበረው አንድ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ፓርቲ ብቻ ሲያገለግሉ የቆዩ የሰራተኛ ማሕበር መሪዎችና የመንግስት አማካሪዎች አግባብ ያለውን የስራ አሰራር ወቅሳችኃል በመባል የታሰሩ ነበሩ። ሌሎችም የቀም እስር ተበይኖባቸዋል። የንግድ ማህበራት ኃላፊዎችም በፖለቲካ አስተያየታቸው ታስረዋል። ጥር 1983 ዓ.ም. (1990) በሰራተኞች ፓሪቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ በተደረገው ለውጥ ብዙዎቹ የሰራተኞች ማሕበርና የንግድ ማሕበራት ኃላፊዎች ከሁለት ወር በኃላ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ የተደረገውን ለውጥ በስራ ላይ እንዲውል ሃሳባቸውን ያቀረቡ አዲስ አበባ ላይ ታስረው ነበር።

ብዙዎች የፖለቲካ እስረኞች በ 1982 ዓ.ም. (1989) እና በ 1983 ዓ.ም. (1990) አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው መካከለኛው እስር ቤት እንደታሠሩና እንዲሁም ሌሎች እስከ መጋቢት 1983 ዓ.ም. (1991) ድረስ የታሰሩ ነበሩ።

የእስረኞቹ ሁኔታ አሰቃቂ ከመሆኑ በላይ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው በመሰቃየት ላይ ይገኙ ነበር። ብዙ እስረኞች የደረሱበት ሳይታወቅ የጠፉ ተገድለዋል።

ግንቦት 1983 ዓ.ም. (1991) ፕሬዚደንት ምንግስቱ ከአገሪቱ ሲያመልጥ በተተካው መንግስት ከተለቀቁት 187 የፖለቲካ እስረኞች ውስጥ 140 ከግንቦት 1982 ዓ.ም. (1989) መንግስቱን ለመገልበጥ የተካሄደውን የወታደራዊ ኩዴታ ተባባሪዎች ናችሁ ተብለው የታሰሩ ናቸው። አዲስ አበባ፣አስመራ፣ እንዲሁም የተቀሩት ከተማዎች ውስጥ የነበሩ የፖለቲካ እስረኞች ከመጨረሻ ግንቦት 1984 ዓ.ም. (1991) በኃላ የእስር ቤቱ ዘበኞች ሲያመልጡ ወይም ደግሞ በተጋዳዮች ተፈተው የተለቀቁ ነበሩ። ሚያዚያ 1983 ዓ.ም. (1991) ኢ.ህ.አ.ደ.ግ ጎንደር ከመግባታቸው በፊት ከ 100 በላይ የሚሆኑ ትግሬዎች በስር ቤት ዘበኞች ተገድለዋል።

## መጥፋትና ህግ ወጥ ግድያ

ፀሃይ ቶሎሳ ባለቤትዋ በሕይወቱ ይኖራል ብላ በተስፋ ትኖራለች (ፎቶ 6 እና 7 ገጽ iii)። ለመጨረሺያ ጊዜ ባልዋን ያየችው ከ 12 ዓመት በፊት አዲስ አበባ ውስጥ ከቤተ ክርስትያን ሲወጣ መሳሪያ በያዙ ሰዎች በግዳጅ ሲወሰድ ነው። ፀሃይ ከጥቂት ሰዓታት በኃላ ተፈታ እንደገና ደግሞ በመጀመሪያ የ 1973 ዓ.ም. (1980) ጀምራ ለ 9 ዓመታት ታስራ ተፈታች። ባልዋ ቄስ ጉዴና ጉምሳ ግን የት እንደደረሰ ሊታወቅ አልተቻለም። የኢትዮጵያ ወንገላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ኃላፊ ነበር (የዓለም አቀፍ ሉተራን ፌዴሬሽን አባል)።

ፀሃይ ቶልሳ የምታሳልፈው ያለችው እርር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የመንግስት ተቃዋሚዎች ተብለው በፖለቲካ ምክንያት ታስረው ከ 1967 ዓ.ም. (1974) በኃላ ኤትዮጵያ ውስጥ "ጠፍተው" የቀሩ የሚያሳልፉት አሰቃቂ ኑሮ አንድ ምሳሌ ነው። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች በጸጥታ ፖሊሶች ተወስደው የት እንደደረሱ የማይታወቁ አሉ።

" መጥፋት " የሚባለው ችግር ለቤተሰቦቻቸው ብቻ ሳይሆን ወዳጆቻቸውንም ስልሚነካ የጠፉትን የት እንደደረሱ ለማወቅ ብዙ ዓመታት ጥረት አድርገዋል። እነዚህ የት እንደደሱ ሳይታወቀ ጠፍተው የቀሩት በሚያሰቅቅ ሁኔታ ያለ ፍርድ በሚስጢር ተገድለዋል።

የጥቂት ሺ ሰዎች መጥፋት ብቻ ነው በመዝገብ ላይ ሰፍሮ የነበረው። ከነዚህም ማንም ሕጋዊ ምርመራ የተደረገለት ሰው አልነበረም። " በቀይ ሽብር " ጊዜ በብዙ መቶ ወይም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የሁለተኛ ደረጃና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የት እንደደረሱ ሳይታወቅ ጠፍተው ቀርተዋል። እነዚህ በጸጥታ ባልደረቦች ጸረ መንግስት እንቅስቃሴ አድርጋችኋል በማለት ወይ ደግሞ መንግሥቱን ከሚቃወሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ህ.አ.ፓ) ጋር ግኑኝነት አላችሁ በመባል በሚስጢር የተገደሉ ነበሩ። በዚያን ጊዜ ብዙዎች የፖለቲካ ተቃዋሚዎች በጸጥታ ኃላፊዎች ያለፍርድ ተገድለው ሬሳቸው ለህዝብ መቀጣጫ ተብሎ በመንገድ ላይ ይጣል ነበር።

ከ 1971 ዓ.ም. (1978) በኃላ የጠፉ ሰዎች ብዛት እየቀነሰ ይሂድ እንጂ ጨርሶ አልጠፋም። ሃላፊነት ያላቸውም ይህን ያለ ፍርድ መታሰርና መጥፋት ለማቆም ምንም እርምጃ አልወሰዱም።

በ 1972 ዓ.ም. (1979) " ጠፍተው " ከቀሩት ፖለቲካዊ እስረኞች ውስጥ በ 1967 ዓ.ም. (1974) የታሰሩ የድሮ ሚኒስትሮችና ባለስልጣኖች (ፎቶ 8 ገጽ ii ተመልከቱ) ሁለት የቤተ ክርስትያን መሪዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ፓትሪያርክ (ፎቶ 9 ገጽ iii) እና የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስትያን መካነ ኢየሱስ መሪ - የመላው ኢትዮጵያኖች ማሕበራዊ ንቅናቄ (መኢሶን) መሪዎች በ 1970 ዓ.ም. (1977) የታሰሩ ይገኙበታል። በደርዘን የሚቆጠሩ ለብዙ ዓመታት የታሰሩ በ 1978 ዓ.ም. (1985) እና 1979 ዓ.ም. (1986) አዲስ አበባ ውስጥ ጠፍተው ቀርተዋል። ከነዚህ ውስጥ የ ኢ.ህ.ን.ፓ አባሎች ለስምንት ዓመት የታሰሩ እንዲሁም ለብዙ ጊዜ የታሰሩ የኦሮሞና የትግራይ ተቃዋሚዎች ደጋፊዎች ተብለው የተጠረጠሩ ይገኙበታል። በኤርትራ

አስር ቤቶች ተመሳሳይ " መጥፋት " የደረሰባቸው ገና ቁጥራቸው መዝገብ ውስጥ አልገባም።

ባለፈው 17 ዓመታት በተለይ ኤርትራና ትግራይ ውስጥ ያለ ፍርድ ወታደሮች የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ይገድሉ ነበር። ያለ ሕግ የፖለቲካ እስረኞችን መግደል በተከታታይ ብረታዊ ግጭት ያለበት ቦታ በወታደሮች ይካሄድ ነበር። መሳሪያ ያልያዙ አርሶ አደሮች ከተጻራሪ ቡድን ጋር ግንኙነት አላችሁ ተብለው በወታደር ክፍሎች ቁጭታቸውን ለመወጣት ይገድሉዋቸው ነበር። ይሄ ቁጭት ለመውጣት መግደል የሚካሄደው ወታደሮች ከጦርነት ተሸንፈው ሲመለሱ ነው። ከፋ የሆነ ድርጊት የተፈጸመው በግንቦት 12 1981 ዓ.ም. (1988) ኤርትራ ውስጥ ሸዕብ የተባለ 60 ኪሎ ሜትር ከማሳዋ ሰሜናዊ ምዕራብ በሚገኝ ቦታ ነበር። እዚህ ቦታ 400 የሚሆኑ አገሩ ተቀማጮች በኢትዮጵያ ወታደሮች ተከበቡ። ከነዚህ ውስጥ 80 የሚሆኑ ጠለቅ ያለ ጉድጋድ ውስጥ አስገብተው በታንክ ሲጨፈለቁ የተቀሩት ደሞ ተረሸኑ። በተጋዳዮች የተያዘ ቦታ ውስጥ የሚኖሩ ብዙ ተራ ሰዎች ተባባሪዎች ናቸው በማለት በኢትዮጵያ የአየር ሃይል ባልደረቦች ይደበደቡ ነበር። በሰኔ 22 1981 ዓ.ም. (1988) ባንድ ጊዜ 1300 የሚሆኑ ትግሬዎች ሀውዜን ውስጥ በአየር ኃይልና በሂሊኮፕተር ተረሽነዋል። ይህ ተ.ሓ.ህ.ት የሚቆጣጠሩት ቦታ አልነበረም።

## መሰቃየት

★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★★

" የኔ መሰቃየት ምርመራ ቦታ እራቁቴን አውጥተው እጆቼን የፍጥኝ አስረው በጥፊ ማጠናገርና በኮረንቲ ግርፋት ተጀመረ። በሁለተኛ ምርመራ ደረጃ እጆቼን አስርው ቀዳዳ ያላቸው በብሎን የሚጠብቁ ሁለት ብረቶች በእጆቼ ማህከል አስገቡ፤ እጆቼን በሁለቱ ብረቶች ማህከል በማጥበቅ ደሜ ቆሞ ጣቶቼ አልንቀሳቀስ አሉ ከጥቂት ጊዜ በኃላ እጆቼ ሶስት አራት ቦታ ተጨፍልቀው እንደማይሰሩ ሆኑ። "

" ከዚህ የባሰው የሶስተኛ ደረጃ ማሰቃየት ደግሞ ትልቅ ጠረጴዛ ውኃ ከሞላ በርሚል አጠገብ ተቀመጠ፤ አራሴን ቆሻሻ ከሞላው በርሚል ውስጥ በመድፈቅ ሆዴ ቆሻሻ ሞልቶ ትን ብሎኝ እስካስታውክ ድረስ ቀጠለ። ቀዝቃዛ እግሬን ገላዬን ገረፉኝ ህይወቴን በመንሳት ራቆቴን ተዘረጋሁ። "

( ይህ በ 1981 ዓ.ም. (1988 ) ለአመንስቲ እንተርናሽናል አንድ የኦሮሞ ተወላጅ ከ 1971 ዓ.ም. (1981 ) እስከ 1980 ዓ.ም. (1987 ) በእስር ቤት የቆየ ያሳለፈው መሰቃየት ምስክርነት ነበር። )

☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆

ከዚህ የሚቀጥለው ከ 1973 ዓ.ም. (1980 ) እስከ 1984 ዓ.ም. (1991 ) ድረስ አዲስ አበባ ሚኒሊክ ቤተ መንግስት ውስጥ " ሳይበሪያ " የሚባል እስር ቤት ጋዜጠኛ ያሳለፈው መሰቃየት ምስክርነት ነው። ይህ ቦታ የደርግ ዋና መስሪያ ቤት ነበረ።

"ያን ቀን በጥፊ፣ በርግጫ እየደበደቡ ከመሰቃያው ክፍል በ 24 ሰዓት ውስጥ 17 ጊዜ ተመላለስኩ። በመጨረሻ በታሰሩት እጆቼና እግሮቼ መሃከል ረጅም እንጨት አስገብተው ቁልቁል በማንጠልጠል አፌን በቆሻሻ የእግር ሹራብ ወትፈው ሁለት ሰዓት ከቆየሁ በኋላ አወረዱኝ።

"ለአምስት ዓመት ተሰቃየሁ። ለብዙ ጊዜ ተንበርክኬ እራመድ ነበር። የጆቼን ጥፍር በሙሉ ነቅለው አሰቃይ ስለነበር ለብዙ ወራቶች እንደ ህጻን ልጅ ሌሎች ይመግቡኝ ነበር። ጆሮዎቼና አይኖቼ በጣም ተጎድተው ነበር። በዚህ ምክንያት ሳንባዬ ተነክቶ ባስጊ ሁኔታ ይገኛል።

"ሳይበሪያ ውስጥ ከዘበኞች ትርፍራፊ ምግብ በ 24 ሰዓት ውስጥ አንድ ጊዜ በዘበኞች ፍቃደኛነት እየበላን እንኖር ነበር። ቤተ ሰቦቼ እንዳይጠይቁኝ ደብቀው ለአምስት ዓመት ቆየሁ። ለቁስላችን መድኃኒት ስላልነበር ግማት አገር ያስለቅቅ ነበር።

"ሳይበርያ ውስጥ የመንፈስ ስቃይ ከአካል ስቃይ የባሰ ነበር። ከአንጎል መሰቃየት አንጻሩን ለመጥቀስ እስረኞች ከተለያዩ 'በርሙዳዎች' (ሚስጥራዊ እስር ቤት) ይደባለቃሉ። እስረኞች ከሌላ እስር ቤት ወደ ሳይበርያ ሲተላለፉ እንደ ልማድ ሆኖ ወድያው ይረሸናሉ። አንዳንድ ጊዜ ሳይበሪያ ያሉትንም ይጨምርዋቸዋል። አዲስ የመጡትንና ነባሮችን በአንድ ላይ ይመዘገባሉ። እስከ እኩለ ሌሊት የሚረሸኑትን ስም ይጠራሉ አንዳንድ ጊዜ አውቀው ለመግደል ስማቸው ያልተመዘገቡትን በመጥራት ያስደነግጥዋቸው ነበር።

☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆☆

የሚቀጥለው ምስክርነት በአንድ የትግራይ ተራ ወታደር ከ 1977 ዓ.ም. (1984) እስከ 1983 ዓ.ም. (1991) ድረስ አዲስ አበባ ውስጥ ማእከላዊ የተባለው የጸጥታ እስር ቤት የተሰቃየ ነው።

"እኔ ሰባት ዓመት ከመንፈቅ በታሰርኩበት ጊዜ የተለያየ መሰቃየት አሳልፌ ነበር። ብዙ ጊዜ በተለያየ በትር ተደብድቤለሁ። ኮረንቲ ያስይዙኝ ነበር ውሃ በሞላ በርሚል ውስጥ ያሰምጡኝ ነበር፣ እግሮቼን አጣራው ላይ አስሮው ቁልቁል ያንጠለጥሉኝ ነበር። እግሮቼን ጥርስ ባለው መሳርያ አጥብቀው በማሰር የደም ስሬ ስለተጎዳ መራመድ ያቅተኝ ነበር። ከመሬት ከፍ ባለ ጠረጴዛ ላይ ወጥረው በማሰር እያሰቃዩ ይታዘቡ ነበር። የተወጠሩትን እጆቼንና እግሮቼን በኮረንቲ እስኪ ደነዝዙ ድረስ ይደበድቡኝ ነበር። አይኖቼን በጨርቅ ሸፍነው በብትርና በኮረንቲ ሽቦ ሕይወቴ እስኪጠፋ ድረስ ይገርፉኝ ነበር። በብትር ከመደብደብ ብዛት ደሜ ፈሶ ለሞት የደረስኩበት ጊዜ ነበር።

"አሰቃዮች ልብሴን አውልቀው ራቆቴን ቀዝቃዛ ወለል ላይ ያስተኙኝ ነበር። በተጨማሪ የሚሰጡኝ ምግብ ለአንድ በሕይወት ለሚኖር ሰው በቂ አልነበረም። የህክምና ቦታና የንጽህና ነገር ሳይወራ ቢታለፍ ይሻላል በጣም አሰቃቂ ነበር።

"በዚህ ምክንያት የተነሳ ዛሬ የአካልና የአንጎል ስቃይ አለብኝ። ያሳለፍኩትን

የእስር ቤት ጊዜ ሳስታውስ እዚህ ዓለም ውስጥ መኖር አስጠልቶኝ እንቅልፍ ሳይወስደኝ እጋደማለሁ። እሱ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቼን ለማገዝ ስራ ስለሌለኝ የገንዘብ ችግር አለብኝ።"

የዚህ አይነቱ ስቃይ ለሁሉም የፖለቲካ እስረኞችና ወንጀለኞች ገና ሲያዙ የሚደረግ የተለመደ አለታዊ ተግባር ነበር። በተለይ ደግሞ ከ 1970 ዓ.ም. (1977 ) እስከ 1991 ዓ.ም. (1978 ) "በቀይ ሽብር" ጊዜ በቀበሌ የጸጥታ ባልደረቦች ይዘወተር ነበር። ከ 1979 ዓ.ም. በኋላ ግን የጸጥታ ባልደረቦች በፖለቲካ ተቃዋሚነት ለታሰሩ እስረኞች እንደሚሰቃዩ በተከታታይነት ለአመንስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት ይደርስ ነበር።

ለብዙ ዓመታት ሁለት አይነት የመሰቃየት አሰራር አስመራና አዲስ አበባ እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች በሚገኘው መሀከለኛው እስርቤት ይዘወተር ነበር። የመጀመርያው የማሰቃየት ዘዴ የተለመደው ውስጥ እግር መግረፍ ነበር። አብዛኞዎቹ ታስረው የተፈቱ ለአመንስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት ሲያቀርቡ ውስጥ እግር መገረፍ የተለመደ ስለሆነ ሳይገልጡት ችላ ብለው ያልፉት ነበር። ሁለተኛው የተለመደው ማሰቃያው ደግሞ አይኖችህን ጨፍነው አፍህን አፍነው እጆችህን የፍጥኝ አስረው ጣራ ላይ በማንጠልጠል ለረጂም ጊዜ ማሰቀየት ነበር። ይህ እንዳይበቃ ደግሞ እጆችህንና እግሮችህን በኤሌትሪክ ሽቦ ይገርፉት ነበር። አንዳንድ ጊዜ ውሃ የሞላ ጠርሙስ አብልታቸው ላይ በማሰር ስቃይ ለመጨመር ጅውጅው ያደርጉታል።

ሌላ አይነት ማሰቃየትም እንዳለ ይነግር ነበር። እስረኞች የነበሩት እንደሚገልጹት በትንሽ ጨለማ ቤት ውስጥ አስገብተው በእርግጫ ራሳቸውን* ጆሮአቸውን* ብልታቸውን ይደበድቡአቸው ነበር። ለአንዳንዶቹም ሽጉጥ እርሳቸው ላይ በመደቀን በሞት ያስፈራሩዋቸው ነበር። አንዳንዶችን ኤሌትሪክ ያስይዙዋቸው ነበር።

ሴቶች እስረኞች ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ስቃዮች ነፃ አልነበሩም እንድያውም በተጠማሪ ያባልግቿቸው ነበር። በ 1963 ዓ.ም. (1970) "በቀይ ሽብር" ጊዜ የታሰሩ ሴቶች እንጨትና የጋለ ብረት ብልታቸው ውስጥ ያስገቡባቸው ነበር።

እስረኞች በተደጋጋሚ ራሳቸውን ቆሻሻ ውሃ የሞላ በርሚል ውስጥ እያጠለቁ ትን እስኪላቸው ወይ ህይወታቸውን እስኪስቱ ድረስ ያስቃዩዋቸው ነበር። አንዳንዶችን ደግሞ የእጆቻቸውንና የእግሮቻቸውን ጥፍሮች ይነቅሉባቸዋል* እጆቻቸውን በብረት አስረው ይጨፈልቁታል* ሹል በሆነ ድንጋይና ሚስማር እንዲሩቃቀ ያደርጉዋቸዋል* ያለ ውሃና ምግብ ለብዙ ጊዜ እንዲቆዩ ያደርጓቸው ነበር። ወንበር ላይ ታስረው ከስርቤት ውጭ በለሊት ብርድ እንዲሰቃዩ ይደረግ ነበር።

## የሞት ፍርድ

ኢትዮጲያ ውስጥ የሞት ፍርድ በህግ የጸደቀና በስራ ላይም የሚውል ነበር። ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በሚገባ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው የተገደሉ ብዛታቸው አይታወቅም ይሁን እንጂ ከነዚ በምሲጥር ያለፍርድ የተገደሉት ጋር ሲወዳደር ቍጥሩ በጣም ዝቅ ያለ ነው። ወታደሮች በደል አድርገው በወታደራዊ ችሎት ተፈርደው የተገደሉ ካሉ ሊታወቅ አይችልም። በግንቦት ወር 12 ወታደሮችና የጦር ሀይል ባልደረባዎች በወታደራዊ ችሎት ተፈርደው ተገድለዋል። እነዚህ ግን መንግስት ለመገልበጥ ሞክራችኋል ተብለው የተከሰሱ ነበሩ። ሕ-ዊ ፍርድ ለማግኘት ሆነ ይግባኝ ለማለት መብት አልነበራቸውም።

60 የሚሆኑት ዮት ወንጀል የፈጸሙ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው እስካለፈው ኅምንት በመሃከለኛው እስርቤት አዲስ አበባ ውስጥ እስከ ግንቦት 1983 ዓጠምጠ (1991) ድረስ ታስረው ይገኙ ነበር። እነዚህ የሞት ፍር ቸው እንድኻኻልላቸው ወይም ምህረት እንደረግላቸው ይግባኝ በማለት ላይ ይገኙ ነበር። በሌላ እስር ቤቶች ውስጥም ሞት የተፈረደባቸው እስረኞች ይኖራሉ።

# የወደፊት ሰብአዊ መብት አጀንዳ

ከግንቦት 1983 ዓ.ም. (1991) ወዲህ በኢትዮጲያና በኤርትራ ሰላም ሰፈነ። ይሁን እንጂ በትንሹ በአንዳንድ ቦታዎች ለጥቂት ወራቶች የ ኢ.ህ.አ.ደ.ግ (የጸጥታ ኋይል) እና የኢትዮጲያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ጎጃም ውስጥ ግጭት አድርገው ኢህአፓ ተሸነፈ። በሌላ ቦታዎችም የጎሳ ግጭት ይታያል በተለይ በሀረርጊ የሚገኙ የኦሮሞ ቡድን መሀከል፥ በምስራቅ ኢትዮጲያ የሚገኙ አፋሮች መሀከል እንዲሁም ዓሰብ የሚገኙ ኤረትራውያኖች መሀከል ናቸው። ይህ ግጭት ረሃብን ለማስወገድ ለሚደረገው ትግል እንቅፋት ሆኖዋል። የአርዳታ ድርጅቶች በኢትዮጲያና ኤርትራ ውስጥ እስከ ስምንት ሚልዮን ህዝብ ረሀብ የሚያሰጋቸው መሆኑን ገለጹ።

በኢትዮጲያ ውስጥ የኢ.ህ.አ.ደ.ገ መንግስት በመቃወም የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን ለመበጥበጥ ነው ተብሎ ሰልፉ በተኩስ ተበተነ። ተመሳሳይ ሰልፎች በአዲስ አበባና በደሴ እንዲሁም በሌላ ክፍለ ሀገሮች ተደርጎ እስከ 20 ሰዎች ተገድለዋል። በሃምሌ 22. 1983 ዓ.ም. (1991) ጊዚያዊ የኢትዮጲያ መንግስት ያጸደቀው እንዲሁም የሁለት ዓመት ጊዚያዊ ህግ ባረጋገጠው "በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት የሰብአዊ መብት የተጠበቀ መሆኑን አረጋገጠ" (አንቀጽ 1)። የሕሊና ነጻነት፥ ሃሳብን መግለጽ፥ ሰላማዊ ስብሰባዎች ማካሄድ ይፈቀዳል። እንዲሁም የሰው መብት እስካልነካ ድረስ ያለ ተጽእኖ የፈለገውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ መደገፍና ፖለቲካ ፓርቲዎች ለመመስረት መብት ይሰጣል (አንቀጽ 1 ሀ እና ለ)። በተጨማሪ "አንድ ብሔርና ብሔረሰብ የራሱን ውሳኔ ሊያደርግ እንደሚችል ያረጋግጣል (አንቀጽ 2)።

በነሐሴ 1983 ዓ.ም. (1991) የተሰበሰቡት ወኪሎች በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ የፖለቲካ ፓሪቲዎች መመስረት፥ ፖለትካዊ ስብሰባዎች ማካዬድ፥ ሰላማዊ ሰልፍ ማካሄድ፥ የሚፈቅድ አዲስ ሕግ አጸደቀ። ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስራቸውን በማጣደፍ ላይ ይገኛሉ። ጥቂቶች ተቃዋሚዎች ገና ውጭ አገር ይገኛሉ። ለመጀመርያ ጊዜ ኢትዮጲያ ውስጥ የሰብአዊ መብት

ድርጅቶች ለቋቋም ችለዋል። ኤርትራ ውስጥ ግዜያዊ መንግስት ማንኛውም የፖለቲካ ቡድን ስራውን ሊያካሂድ ይችላል ይበል እንጂ እስከ አሁን ድረስ ያለ ህ.ግ.ሓ.ኤ በስተቀር የፖለቲካ ማሕበር የለም። አንዳንድ የህ.ግ.ሓ.ኤ ተቃዋሚዎች ውጭ አገር ይገኛሉ።

ኢትዮጲያና ኤርትራ ውስጥ የቆሙት አዲስ መንግስቶች የቀድሞውን መንግስት ባለ ስልጣኖችና የሰራተኞች ማሕበር ሀላፊዎች እንዲሁም በሺ የሚቆጠሩ በጠሩነት ያልተማረኩ ወታደሮች ማለት ባህር ኃይል፣ የአየር ሃይል፣ ፖሊሶች፣ የእስር ቤትና የጸጥታ ባለስልጣኖች አስረዋል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በ ኢ.ህ.አ.ደ.ን እና በ ህ.ግ.ሓ.ኤ. የተማረኩና ወደ ውጭ አገር ሸሽተው የነበሩ ወታደሮች ወደ አገራቸው መመለስ ወደ ፍጻሚው ነው። የበላይ ባለ ስልጣኖች ግን ገና እስር ቤት ይገኛሉ።

ባለስልጣኖች እንደገለጹት እስረኞች በጦርነት ጊዜ ባደረጉት ወንጀል እና የሰብአዊ መብት መጣስ መሰረት አድልዎ የሌለበት ፍርድ እንደሚሰጣቸው ገለጡ። አንዳንዶች በኢትዮጵያና በኤርትራ የተፈቱ አሉ እንጂ ተከሶ ወደ ፍርድ የቀረበ የለም። እስካሁን ድረስ እንደሚታወቀው መሰቃየትና መጥፎ እንክብካቤ የተደረገለት እስረኛ የለም ይሁን እንጂ የአንዳንዶች እስር ቤት ሁኔታ አጥጋቢ አይደለም። እያንዳንዶች የት እንደታሰሩ አይታወቅም።

እነዚህን ሕጋዊ በሆነ አገባብ ወደ ፍርድ እንዲቀርቡ ጽሑፍ እየተነደፈ ነው። የ ኢ.ህ.አ..ግ ግዜያዊ መንግስት እንዳመለከተው ዓለም አቀፍ ሕግ ተከትሎ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች እንደ አመንስቲ ኢንተርናሽናል ታዛቢ ልኮ የሚከታተለው ሕጋዊ የሆነ ፍርድ የሚሰጣቸው መሆኑን አስታውቀዋል። አህንም በጋዜጣና ስብስባዎች ተመርተው ማሰቃየትና " ማጥፋት " በተለይ ከ 1971 ዓ.ም. (1977) እስከ 1971 ዓ.ም. (1978) በ " ቀይ ሽብር " ጊዜ ያስገቡ ሰዎች እጃቸውን ያስገቡ ሰዎች ይታሰራሉ። ከነዚህ ሰብአዊ መብት ጥሰዋል ተብለው ከታሰሩት ከ1973 ዓ.ም. (1980) በኋላ የራሳቸው መብት ተጥሶ ገና አሁንም ባሳለፉት መሰቃየት የአንጎል ችግር ያለባቸው ናቸው።

አመንስቲ ኢንተርናሽናል አሁን በኢትዮጲያና በኤርትራ ውስጥ በእስር ቤት የሚገኙት እስረኞች የታሰሩበት ምክንያት በፖለቲካ አስተያየታቸው ነው ወይስ በወደቀው መንግስት በነበራቸው ስልጣን ለማረጋገጥ ጉዳዩን እየተከታተለ ነው።

ኤረትራ ውስጥ ህ.ግ.ሓ.ኤ ጊዚያዊ መንግስት ያለ ማስታወቂያ 80000 ኢትዮጲያውያን ምርኮኞች እና 45000 ኤርተራውያንኖች ያልሆኑ ተራ ህዝብ አስወጣ። አብዛኛወቹ የወታደሮች ቤተሰቦች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የቀድሞው መንግስት ፓርቲ ባለስልጣኖችና የአማርኛ ቋንቋ አስተማሪዎች (ትግርኛ ቀርቶ በአማርኛና አረበኛ ተተክቶ ነበር) ናቸው። ጥቂት ቆሳቁስና ገንዘብ ሰጥተው ሸኝዋቸው። ብዙዎች ጊዚያዊ እርዳታ ወደ ሚሰጥበት ወደ ደቡብ ጊዜያዊ መጠለያ ሲሄዱ ሞተዋል።

በሐምሌ 1983 ዓ.ም. (1991) አመንስቲ ኢንተርናሽናል አዲስ አበባን ጎበኙዋት። ለብዙ ዓመታት የሰብአዊ መብት ድርጅት ጥላቻ የነበረው መንግስት ከተገለበጠ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ ሆኖ የፈለገበት ቦታ ደረሰ። እነዚም ለብዙ ዓመታት በፖለቲካ ምክኒያት ታስረው እንዲፈቱ ይደክምላቸው ከነበሩት ጋር ተገናኙ። እዛም የታወቀውን ሦስት እስር ቤቶች ቁጥር የሌላቸው የፖለቲካ እስረኞች የሚታሰሩበትና የሚገደሉበትን ፊልም እንዲያነሱ ተፈቀደላቸው። እነዚህም ማእከላዊ የጸጥታ እስር ቤት፥ተጨማሪ ስሙ "በርሙዳ ትሪያንግል" ተብሎ የሚጠራው የድሮ አውሮፕላን ማረፊያ አጠገብ የሚገኙ ናቸው (ፎቶ 1.2.3. እና 4 ገጽ 1 እና 2)።

## የወደፊት ሰብአዊ መብት አጀንዳ

እነዚህ አዲሶች ጊዜያዊ መንግስቶች ኢትዮጲያና ኤርትራ ውስጥ ለወደፊቱ ብዙ ሃላፊነት ፈተናዎች ይጠብቃቸዋል። ከሁሉ ከፍ ያለው ሀላፊነት ደግሞ ለብዙ ዓመታት ሲካሄድ የቆየው የሰውን መብት አለማክበር መቅሰፍት ማስወገድ ነው። ይህንን በስራ ላይ ለማዋል አዲሶቹ መንግስቶች ለሰብአዊ መብት ቅድሚያ ሰጥተው መንቀሳቀስ አለባቸው። አመንስቲ ኢንተርናሽናል ለኢትዮጲያ

መሸጋገርያ መንግስትና ለኤርትራ ጊዜያዊ መንግስት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነጥቦች ተመልክተው ባፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ ያሳስባል።

## 1. የህሊና እስረኞችን አለማሰር

ማነኛውም ሰው በፖለቲካ አስተያየቱ* በእምነቱ* በዘሩ ምክንያት እንዳይታሰር ማረጋገጥ። እነዚህን የሕልና ተቃዋሚ ለማሰር ብለው የወጣውን ሕግ በአፋጣኝ መሰረዝ።

## 2. ለማያዳላ ፍርድ ዋስትና

በፖለቲካ ምክንያት ለታሰሩ በፍጥነት ፍርድ እንዲደረግላቸውና መፈታት ያለባቸውን መፈታታቸውን ማረጋገጥ። በወደቀው መንግስት ውስጥ ስልጣን የነበራቸው* ባለስልጣኖችና ሌሎች ተባባሪዎች* በአለም አቀፍ ሕግ መሰረት ሙብታቸው እንዲታወቅላቸው ያስፈልጋል። በመንግስቱ ጊዜ እንደነበረው እስረኞችን በሚስጥር ፈርዶ ማሰቃየት ፈጽሞ መመለስ እንደሌለበት። አሁን ለታሰሩት አዲስ እስረኞች በዓለም አቀፍ የጸደቀ ሕግ መሰረት የማያዳላ ፍርድ እንዲደረግላቸው የሚቀጥለውን ነጥቦች ያቀርባል።

- የመረጡትንና የራሳቸውን ጠበቃ እንዲመርጡ
- ፍርዳቸው ህጋዊና ለህዝብ ክፍት መሆን አለበት
- በመሰቃየት ጊዜ የተገኘ ቃል ተቀባይነት እንዳይኖረው ይሁን እንጂ ማሰቃየት
  ለሚያካሂዱት የማሰቃየታቸው ምስክር ሊሆን እንደሚችል
- የተፈረደባቸው ሁሉ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊሉ እንደሚችሉ ማረጋገጥ።

## 3. የተገለበጠ አስተዳደራዊ አሰራት

በሚስጥር አስር ከሰው ጋር እንዳይገናኙ ማድረግ መከልከል አለበት። እነኚህ ሁለት ሁኔታዎች የሰብአዊ መብት መጣስ ባለፉት ጊዜያቶች እስረኞችን ማሰቃየትና "ማጥፋት" እንደሚያስከትልና ቤተሰቦችም የታሰሩባቸውን ሁኔታቸው ለመከታተል ዋናዋቹ ተግባሮች ነበሩ። የመንግስቱ መንግስት ከተገለጠ ወዲሕ ለስድስት ወር ያህል የታሰሩት በሺ የሚቆጠሩ የድሮ የሲቪልና የሚሊተሪ ባለስልጣኖች አስራታቸው በተሎ መጨረስ አለበት። ተፈርደባቸው ጥፋታቸውን አውቀው መታሰር አለባቸው ወይም ደግሞ መፈታት አለባቸው። ስለዚህ የሚከተሉት ለውጦች እንዲደረጉ ያሳስባል።

- ህጋዊ ያልሆነ የፖለቲካ እስረኞች በሚስጥር ማሰር እንዲቀር በጥብቅ መከታተል
- እስር ቤቶች ሕጋዊ ሆኖው ባፋጣኝ በህዝብ እንዲታወቁና የሚታሰሩበት ቦታ በህግ የታወቁና ተገቢ የእስር ቤት አስተዳደር የሚከተሉ መሆን አለባቸው።
- ሰዎች ሲታሰሩ ለምንና በየተኛው ሕግ እንደታሰሩ ባፋጣኝ ማወቅ አለባቸው። ቤተሰቦቻቸው ደግሞ ስለ እስረኞቹ ሁኔታ ማወቅ እንዳለባቸው።
- ያንዳንዱ በከተማና በገጠር የሚገኙ ባለስልጣኖች ያሰሩዋቸውን ሰዎች ስምና አድራሻ በመደበኛ መዝገብ አስፍረው መያዝ አለባቸው ይህ ደግሞ ለሕጋዊ ወኪሎች ቤተሰቦች ጠቃሚ ነው።
- እስረኞች ሁሉ ባፋጣኝ ፍርድ ቤት ቀርበው ካልተፈረደባቸው በስተቀር መለቀቅ አለባቸው። የታሰሩት ሆነ ቤተሰቦቻቸው የታሰሩበትን ምክንያት ለፍርድ ከማቅረባቸው በፊት የታሰሩበትን ሁኔታ የሚከራከሩበት መንገድ መኖር አለበት፤ ለምሳሌ በመሰረት ሕገ መንግስት ሀቢስ ኮርፑስ (habeas corpus)

## 4. ማሰቃየት መቅረት አለበት

መሰቃየት ከእንግዲህ ወድያ ፈጽሞ በስራ ላይ መዋል የለበትም። እስረኞች ከማሰቃየትና ጨካኝ ሰብአዊ ያልሆነ አያያዝ ወጥተው ሕይወታቸውን የሚከላከሉበት መንገድ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። እነዚያ እስረኞች የሚያሰቃዩ ደግሞ ኃላፊነታቸውን ተሸክመው ለፍርድ መቅረብ አለባቸው። ማንኛውም እስር ቤት የሚሰራ ሰው እስረኞች ማሰቃየትና ማለፋለፍ ክልክል መሆኑንና ያለ አገባብ እስሮኞችን ማንገላታት ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን መግለጫ መሰጠት አለበት። ማንኛውም ሰው በማሰቃየት የተጠረጠረ ሰው እስረኞች ቦታ ፈጽሞ መስራት የለበትም።

ይህንን በስራ ላይ ለማዋል የሚያማክር የማያጋራ ነጻ የሆነ የምርምር ኮሚሽን ያንን በመንግስቱ ጊዜ የነበረውን ማሰቃየትና የጸጥታ ክፍል እስር ቤቶች አጣርቶ የሚከታተል መኖር አለበት። ይህ ኮሚሽን የአሰራር ዘዴውንና ተመራምሮ የሚያገኘውን ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት። ታስረው የነበሩትንና ሌሎች ምስክሮች ከነሱ ጋር ተባብረው እንዲሰሩ ማበራታት አለባቸው። እነዚህን የሚተባበርዋቸውን ምስክሮች የማስፈራራትና የበቀል መውጭያ ችግር እንዳያጋ ጥማቸው በሚገባ መከላከል አለባቸው። ያለ አገባብ ማሰቃየት የሚደረግበት ቦታ በማጥፋት ሄደው ነገሩን ማጥናት አለባቸው። ለማሰቃየት ምክንያት የሆነውን ነገር ተመራምሮና አጥንቶ መሰቃየት ጨርሶ እንዲጠፋ የሚሻሻልበት መንገድና አስተያየት ማቅረብ አለበት።

የአስተዳደር ኃላፊዎችና የፍርድ ቤት ባለ ስልጣኖች ህጋዊ ያልሆነ ማሰቃየት እየተካሄደ መሆኑን ሲነገራቸውና የኮሚሽኑ ውሳኔ ሲቀርብላቸው በፍጥነት ነገሩን መከታተል ይገባቸዋል። ለወደፊቱ እንዲታሰብበት የሚያስፈልገው እስረኞች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ መሰቃየታቸውን ከገለጹ ደኞች በፍጥነት እንዲመረመር ትእዛዝ እንዲሰጡ ነው። የተሰቃየው የእስረኛው ሰውነት በሐኪም ተመርምሮ ከሱ መሰማት አለበት። ያለ አገባብ በማለፋለፍ ወይ ደግሞ በሌላ አገባብ የተገኘ ኑዛዜ እስረኛው በሕግ ተቀባይነት እንደሌለውና

አስረኛው በሰጠው ቃል መሰረት አስራት መራዘም እንደሌለበት።

## 5. "የጠፉት ሰዎች" ሁኔታ ማጣራት

በእስር ቤት አሉ እየተባሉ የት እንደደረሱ ያልተወቀ መኖራቸውንና አለመኖራቸውን የሚከታተል ነፃ የምርመራ ኮሚሽን መቋቋም አለበት። ኮምሽኑ ምስክር ብሎ የጠራቸው "ሰው የጠፋባቸው" ቤተሰቦች ጭምር ቢ.ም በቀል ማስፈራሪያና አመጽ እንዳይደርስባቸው መከላከያ እንዲደረግላቸው ያስፈልጋል። በኮሚሽኑ ተጣርቶ የቀረበ ማስረጃ ሁሉ በአስቸካይ ሕዝቡ እንዲያውቀው ተደርጎ አስረኞች በሚስጥር ለማጥፋት ሃላፊነት ያለባቸው ሰዎች ከሕግ በፊት መቅረብ አለባቸው።

## 6. የሞት ቅጣት ፍርድ ማስቀረብ

ይህ አዲስ መንግስት ባፋጣኝ የሞት ቅጣት ለሆነ ወንጀል ፈጽሞ ማስቀረት አለባቸው። የመጀመርያ እርምጃ መውሰድ ያለባቸው የሞት ፍርድ የተበየነባቸውን ሰዎች ከመግደል ማዳን ነው። የቀድሞው ባለስልጣኖችና የወታደር አላፊዎች ባደረጉት "የጦርነት ወንጀልና ሰብአዊ መብት መጣስ" አሁን እስር ቤት የሚገኙ ከባድ ወንጀል ቢፈጸሙም በሞት ፍርድ መቀጣት የለባቸውም።

የሞት ቅጣት ጨካኝና ሰብአዊ ያልሆነ የመኖርን መብት የሚጥስ ስለሆነ ኣመንስቲ ኢንተርናሽናል ለሆነው ወንጀል የሞት ቅጣት እንዳይደረግ ይቃወማል። የሞት ቅጣት መላሽ የሌለው በቀል ለመመለስና በሚያዳላ ፍርድ ያለማስረጃ የሚደረግ ስለሆነ ነው። የሞት ፍርድ ወንጀል እንዳይፈጸም የሚያግድ ቅጣት እንደሆነ ምንም ማስረጃ የለም።

## 7. ሕገ ወጥ ግድያ መቅረት አለበት

ሁሉም ወታደሮችና የጸጥታ ባልደረባዎች ያለ ህግ ሰው መግድል ወንጀል እንደሆነ በሚገባ እንዲገጽላቸው ያስፈልጋል። የዚህ ዓይነት ትእዛዝ ከበላያቸው ሲመጣ ትእዛዙን አለመቀበል ብቻ ሳይሆን እንደዚህ አይነት ሕገ ወጥ ትእዛዝ ለሚሰጡ ሀላፊዎች እርምጃ እንዲወሰንባቸው ለበላያቸው መንገር እንደሚያስፈልግ።

የፖለቲካ እስረኞችና የጦርነት ምርኮኞች ወይ ደግሞ ሰላማዊ ሕዝብ ባለፈው ጊዜና ለወደፊቱ ሕገ ወጥ ክሶች በሙሉ በሁሉ ወገን ተመርምሮ የተደረገው ግድያ ሕጋዊነት ወይም ሕገ ወጥነት አድልዎ በሌለበት ምርመራ መጣራት አለበት። ሕጋዊ ያልሆነ ግድያ ያደረጉ ወይ ግድያው እንዲደረግ ትእዛዝ ያስተላለፉት ለፍርድ መቅረብ አለባቸው።

## 8. ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ማጽደቅ

ይህ የመሸጋገሪያ የኢትዮጲያ መንግስት ሰብአዊ መብት ለመጠበቅ የማያወላውል ግዳጅ ወስዶ መሰረታዊ ዓለም አቀፍና አሕጉራዊ ያሰራር ዘዴዎችን ማጽደቅ አለበት። ይህንን ለማድረግ በሐምሌ 1983 ዓ.ም. (1991) የተደረገው የመሸጋገሪያ ስምምነት ሙሉ ፈቃድ ሰጥቶታል።

- ዓለም አቀፋዊ ስምምነት በሲቪልና ፖለቲካዊ መብት ከሁለት አማራጭ ስምምነቶች ጋር
- የአፍሪቃ ሰብአዊና ሕዝባዊ መብት ቻርተር
- ስብሰባ አንጻር ማሰቃየትና ሕዝባዊ መብት ቻርተር
- 1970 ዓ.ም. (1977) የተጨመረ ፕሪ ቀጥር 1 እና ቀጥር 2 በ 1942 ዓ.ም. (1949) ጀነቫ ላይ በተደረገው ስብሰባ።

ምንም እንኳ የኤርትራ ሽግግር መንግስት ዓለም ዓቀፍ ታዋቂነት አያገኝ ወይም

ደግሞ የተባበሩት መንግስታት አባል አይሁን እንጂ መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች የሚያስጠብቁ ስምምነቶችን እንደተቀበለች የሚያረጋግጥ መግለጫ እንዲሰጥ ጥሪ ተደርጎለታል።

ይሄ መግለጫ ከዛ 58 ገጽ ጽሁፍ (4,240 ቃላት) ኢትዮጲያ፣ የአረሚናዊ ጭቆና መጨረሻ ዘመን አዲስ ዕድል ለሰብአዊ መብት ( AI Index: AFR 25/05/91) ከሚለው ተጣርቶ በአመንስቲ ኢንተርናሽናል ግንቦት 31, 1982 ዓ.ም. (1991) የቀረበ ነው። ማንኛውም ሰው ተጨማሪ መግለጫ የሚፈልግ ወይም በተጠቀሱት ጉዳዮች ለመውሰድ የሚፈለግ ሁሉ ጽሁፍን ለማግኘት ሊጠይቅ ይችላል።

አመንስቲ ኢንተርናሽናል ከመላው ዓለም በፈቃዳቸው የሚያገለግሉ ንቅናቄ ሆኖ ስራው ደግሞ የህዝብን መሰረታዊ ሰብአዊ መብት በመንግስት እንዳይጣስ መከላከል ነው። ትኩረት የሚደረግላቸው ዋናዎቹ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

- የሕሊና እስረኞችን መፍታት፣ - በተለያዩ ቦታወች ብዙ ሰዎች በእምነታቸው፣በዘራቸው፣ በቋንቋቸው መሰረት ህውከት ወይም ረብሻ ሳያደርጉ በእስር ቤት ይገኛሉ።
- ማዳላት የሌለበት ፈጣን ፍርድ ለፖለቲካዊ እስረኞች
- የሞት ቅጣት፣ ማሰቃየት፣ እስረኞችን በጭካኔ መያዝ ማስቀረት
- ያለ ሕግ መግደልና "ማጥፋት" ማስቀረት

አመንስቲ ኢንተርናሽናል በተጻራሪዎች ቡድን የሚደረገውን አፈና፣ ማሰቃየት፣ በፍቃድህ እስረኞችን መግደል ይቃወማል።

አመንስቲ ኢንተርናሽናል እንደሚያምነው ሰብአዊ መብት የማይሸጥ የማይለወጥ ሆኖ በመላው ዓለም የተከበረውን የሰብአዊ መብትና ሌሎች ዓለም አቀፋዊ መሰረቶች ወደፊት እንዲራመድ የሰብአዊ መብት ትምህርትና ስምምነቶች ዘመቻ ያካሂዳል።

ኣመንስቲ ኢንተርናሽናል ከመንግስት፣ ከፖለቲካ ተጽእኖ፣ ከሃይማኖት ነፃ የሆነ ድርጅት ነው። የማንኛውም መንግስት የፖለቲካ አሰራር አይደግፍም አይቃወምም እንዲሁም ሰብአዊ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ለሚጥሩላቸው እስረኞች ያላቸውን አስተያየት አይደግፍም አይቃወምም። የመንግስቱ ስነሀሳብ ሳይመለከት ስራው ለያንዳንዱ ሰው ሰብአዊ መብቱ እንዳይነካ መጠበቅ ነው።

አመንስቲ ኢንተርናሽናል አገሮችን ባላቸው የሰብአዊ መብት መገንዘብ አይመዝናቸውም ይሁን እንጂ አገሮችን ሳያወዳድር የሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ ያተኩራል።

አመንስቲ ኢንተርናሽናል ከ 1,100,000 በላይ የሆኑ ጸሁፎች የሚከታተሉና ገንዘብ የሚያበረክቱ በ 150 አገሮችና ቦታዎች ውስጥ አባሎች አሉት። በተጨማሪም ከ 6,000 ተራ ቡድኖችና ከ 70 በላይ አገሮች ከአፍሪቃ፣ አሜሪካ፣ አሲያ፣ ኢሮጳና መካከለኛ ምስራቅ ያጠቃልላል። ከወገንነት ነፃ ለመሆን የሆነ ቡድን አገሩ ያልሆነ ቦታ በጆግራፋዊ አቀማመጡና ፖለቲካዊ ድብልቅነቱ ተመርጦ ይመደባል። ምርመራ ስለ ሰብአዊ መብት መጣስ በዓለም አቀፍ አመንስቲ ኢንተርናሽናል ሰከረታሪዎቹ ይካሄዳል። አንድ ክፍል፣ ብድን ወይም አባል ስለ እግራቸው ምልከት እንዲሰጡ አይገደዱም እንዲሁም የሆነ ክፍል፣ ቡድን ወይ ማህበርተኛ በአለም አቀፍ ማሕበሮች ስለ አገራቸው የሚወስደው እርምጃና የሚሰጠው ቃል ሃላፊነት የለውም።

አመንስቲ ኢንተርናሽናል ከተባበሩት መንግስታት የቀጠባና ማህበራዊ ቆንስል፣ የተባበሩት መንግስታት ትምህርትና ባህላዊ ማሕበር፣ የአውሮጳ ቆንሲል፣ የአሜሪካ መንግስት መንግስት ማሕበር፣ የተባበሩት የአፍሪቃ ማሕበርና የውስጠ ፓርላማ ሕብረት መልካም ዝምድና አለው።

አመንስቲ ኢንተርናሽናል ስራዋን የምታከናውነው ጽሑፎችዋን ከሚከታተሉና ከመላው ዓለም ያሉት አባሎች ስጦታ በማግኘት ነው። ከመንግስታት ስጦታ ለማግኘት አታስበውም አትቀበልም። ነፃነትዋን ለመጠበቅ ሁሉም ስጦታወች በአለም ቆንሲል መምርያ መሰረት በጥብቅ ትከታተለዋለች።